## ስያሜ

**DNA** በማናቸውም ሕይወት ባላቸው ፍጥረታት ውስጥ የሚገኝና ማንነትን የሚለይ ንጥረ ነገር ሲሆን ይህም የማንነት መለያ መረጃ (Genetic Information) ከትውልድ ወደ ትውልድና ከወላጅ ወደ ልጅ የሚተላለፍ ነው፡፡
የዚሁ ንድፈ-ሃሳብ ተመሣሣይ ነገር በመንፈሣዊ ዓለምም መገኘቱ አስገራሚ ነገር ነው። ይኸውም፣ በእግዚአብሔር ዘንድ አስቀድሞ የነበረውና የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን የወረሰችው መንፈሣዊ ማንነት፡- ደቀመዝሙርነት፣ ኅብረትና ወንጌልን በመስበክ መንግሥቱን ማስፋት በመሆኑና እነኚሁ ቃሎች በእንግሊዝኛ ሲቀመጡ፡

| | |
|---|---|
| ደቀመዝሙርነት | **D**iscipleship |
| ሕብረት | **N**etworking |
| ወንጌልን ማዳረስ | **A**dvancement ይሆንና |

የቃሎቹን የመጀመሪያ ፊደላት ተወስደው ሲገጣጠሙ ነው DNA የተሰኘውን "ምሕጻረ ቃል" ያስገኙትና የአገልግሎቱን መጠሪያ ለመሆን የቻለው። የዚህ የተፈጥሮ ሣይንስ አስተሣሰብ ከመንፈሣዊው የውርርስ ባሕሪይ ጋር መመሣሰሉ በአገልግሎቱ ፊት እግዚአብሔር ለመኖሩና ወቅታዊም ለመሆኑ እንደ አንድ ማረጋገጫ ተወስዷል።



ደቀመዝሙርነት | ሕብረት | ወንጌልን ማዳረስ

## የDNA ቦርድ

መጋቢ ታምራት ኃይሌ– ድሬክተር

⇒ አገልግሎቱ
- በአሜሪካ (በካሊፎርኒያ) በኢትዮጵያና በደቡብ አፍሪካ
ተመዝግቧል

- የማስተባበሪያ ማዕከላት፡
- ጠቅላላ ጉባኤ
- አስተዳዳሪ ቦርድ
- አስተባባሪዎች አሉት።

## ደቀመዝሙርነት

መጽሐፍ ቅዱሣዊ ደቀመዝሙርነት በዋናነት የባሕሪ ግንባታና የሕይወት ለውጥ ላይ ያተኩራል፡፡ የደቀመዝሙርነት ትምህርትም ምረቃ የሌለውና ከልደት እስከ ስንብት (ሞት) ድረስ የሚሄድ፣ የማያቋረጥ ሂደትና የእድገትና የለውጥ ጉዞ ነው። በሣይንስ ዓለም Evolution የማያቋርጥ ጉዞ ነው እንደሚባለው ሁሉ በክርስትናም እንዲሁ ከዳግም ልደታችን ጀምሮ በየቀኑ በለውጥ ሂደት ውስጥ እንጓዛለን። መጽሐፍ ቅዱስ "ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን" (2ቆሮ 3፡18) ይላልና።

በደቀመዝሙርነት የምንቀረጽበት ህይወት የእግዚአብሔር ሕይወት ሲሆን ይህም ሕይወት የባሕሪ ልጁ በሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ታይቷል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስም "ከእኔ ተማሩ" ባለበት ትዕዛዙ ከአባቱ የወረሰውን ባሕሪይ ተከታዮቹ እንዲወርሱ አጥብቆ አሣስቧል፡፡ የመጀመሪያ ምዕተ-ዓመት ቤተክርስቲያን ይህንን የክርስቶስን የባሕሪይ DNA ያሣየች ቢሆንም ወደ ቀጣዮቹ ትውልዶች በተሟላ ሁኔታ የተላለፈ አይመስልም፡፡ ማስረጃው ዛሬ ዓለም - አቀፏ የክርስቶስ አካል የምትገኝበት ቀውስ ነው፡፡

ደቀመዝሙርነት፡- የተለወጠ፣ ክርስቶስንና የቀደሙትን የዕምነት ቤተሰቦች ህይወትና ኑሮ የሚመስል፣ እግዚአብሔርን የሚያከብር፣ የወንጌልን መልዕክትና ተልዕኳችንን የሚመጥን ሕይወት መኖርና ማሳየት፣ በጽድቅ ኑሮ ኃጢአተኛውን ዓለም መኮነን፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ላይ ሆኖ ያስተማረውን የትህትና (የብጽዕና) ትምህርትና ኑሮ በየዕለቱ ሕይወት መተርጎም ነው፡፡

የዚህ አገልግሎት ተልዕኮም ይኼ DNA ከተቋረጠበት እንዲቀጥል፣ ሰዎች የዕውነት ዳግም እንዲወለዱ (ከተወለዱ DNAው የግድ ስለሚኖር) በዚህ ማንነት እንዲያድጉና ለቀጣይ ትውልድ እንዲያወርሱ ማሣሰብ ነው።



## DNA

**DNA** የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት በ2009 (እ.አ.አ.) ተጸንሶ በ2019 ተወልዶና በ2021 በካሊፎርኒያ ስቴት ሕጋዊ ፈቃድ ያገኘና በቤቴል ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ባርኮት መንፈሣዊና የማኅበረሰብ ልማት አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ አትራፊ ያልሆነ ተቋም ነው፡፡

**ራዕይ**፡- በክርስቶስ የሕይወትና የአገልግሎት ሞዴልነት የታነጹና በፍቅር ገመድ በአንድነት ተሣሥረው የወንጌሉን የምሥራች ላልሰሙ ለማሰማት የሚተጉ ዕውነተኛ ደቀመዛሙርትን በማፍራት በዘመኑና በትውልዱ ላይ የጽድቅ ጫና መፍጠር የቻሉ ጠንካራ አብያተክርስቲያናት በዝተው ማየት፡፡

**ተልዕኮ**፡- ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መንፈሣዊና አካላዊ አንድነታቸውን እያጠነከሩ የዕሁድ መድረካቸውን ጨምሮ ጠቅላላው የእረኝነት እንክብካቤያቸው የአባላቶቻቸውን ሕይወት በደቀመዝሙርነት ባሕሪ በማነጽና መንፈሣዊ ትጥቅ አስታጥቀው ለወንጌል በማሠማራት ላይ እንዲያተኩሩ በትምህርትና በሥልጠና፣ እንዲሁም በምክርና በማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ ታላቁን ተልዕኮ እንዲያሣኩ መርዳት፡፡

**ግብ**፡- አዲስ ኪዳን በሚያስተምረን በነቢያትና በሐዋሪያት መሠረት ላይ በአንድነት የቆመች፣ የውስጥ ንጽሕናዋ መንፈስ ቅዱስን የሚማርክ፣ የውጭ ምሥክርነትዋ ደግሞ ዓለምን የሚማርክ፣ የነቢይነትና የክህነት ሚናዋን በተገቢው የምትጫወት፣ ተሰሚነትና አስሚነት ያላት የክርስቶስ ቤተክርስቲያን መገንባትና ለመነጠቅዋ ቀን ማዘጋጀት።

## ተግባር

### መንፈሣዊ

**DNA አገልግሎት፡-** መጽሐፍ ቅዱሳዊ ደቀመዝሙርነትን በትውልዱ ውስጥ ማስረጽን መሠረትና ግብ ያደረገ የደቀመዝሙርነት ትምህርት፣ የመዘምራንና የአምልኮ መሪዎች ትምህርት፣ የጋብቻና ቤተሰብ ትምህርት፣ የመሪነት ትምህርት፣ የዓይነተኛ ቤተክርስቲያን ምንነት ትምህርት፣ የመንፈስ ኅብረትን በአጥቢያ በክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ ለማጎልበት የሚረዳ ትምህርት፣ የጸሎት ትምህርት ስልታዊ የወንጌል ሥርጭት ትምህርትና ሌሎችንም አስፈላጊና ወቅታዊ ትምህርቶችን ይሰጣል።

**DNA አገልግሎት ፡-** በተለይም ከኢትዮጵያ ውጪ የሚገኙና በአንድ አካባቢ ያሉ የኢትዮጵያውያንና የኤርትራውያን አብያተ ክርስቲያናት የጋራ ኅብረት ባልመሠረቱበት እንዲመሠርቱ የተመሠረቱ ኅብረቶችም እንዲጠናከሩ ድጋፍ ይሰጣል።

**DNA አገልግሎት፡-**ወንጌልን በዓለም ዙሪያ ለማዳረስ የተሰማሩ አብያተ ክርስቲያናትንና የወንጌል አገልግሎት ተቋማትን ያግዛል፣ ሚሲዮናዊ ተልዕኮ እንዲፋጠንም በተቻለው ሁሉ ይደግፋል።

### ማኅበረሰባዊ -

#### ውሀ

**DNA አገልግሎት፡-**ከመንፈሣዊ አገልግሎት ጎን በኢትዮጵያ ገጠር አካባቢ የሚኖረውና የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ያላገኘው ኅብረተሰባችን ንጹህ የመጠጥ ውሃ እንዲያገኙ የበኩሉን አስተዋጽዖ ያደርጋል።

#### ትምህርት

**DNA አገልግሎት፡-**በአቅም እጦት ምክንያት የቀለም ትምህርታቸውን እስከ ዘለቄታው ለመከታተል ተግዳሮት ያለባቸውን ልጆችና ወጣቶች አቅሙ የፈቀደለትን ያህል ለማገዝ ጥረት ያደርጋል፡-

- ◊ በደቡብ ክልል ሐዲያ ዞን ሚሻ ወረዳ በኮዋዳ ቀበሌ ከ 30 ዓመታት በፊት የተተከለውን ትምህርት ቤት በቋሚነት ይደግፋል
- ◊ በሌሎችም የገጠር ከተሞች በከፍተኛ ነጥብ ወደ ለሁለተኛ ደረጃና ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚያልፉ ተማሪዎች ለትምህርት ወደ ከተማ ሲመጡ ማረፊያ ቦታ (ሆስቴል)በማዘጋጀት ትምህርታችውን ያለ ስጋት በመከታተል ለውጤት እንዲበቁ ድጋፍ ያደርጋል።
- ◊ በሰሜን ኢትዮጵያ (ወሎ) ገጠራማ አካባቢ "የዛፍ ጥላ ሥር" ት/ት ቤቶች መደበኛ የትምህርት ቤት (መጠለያ) እንዲኖራቸው ያግዛል

#### ጤና

DNA በገጠሮች አካባቢ የሚንቀሳቀስ አነስተኛ ተንቀሣቃሽ (Mobile) ክሊኒክ በማደራጀት ኅብረተሰቡ መሠረታዊ ሕክምና፣የግልና የአካባቢ ንጽሕናና የስነ-ተዋልዶ (የቤተሰብ ምጣኔ) ትምህርት እንዲያገኙ ደጋፍ ያደርጋል።

## የአገልግሎት ጅምር

**DNA አገልግሎት፡-**በአሜሪካን አገር ሕጋዊ ሆኖ እንዲንቀሣቀስ የሚያስችለውን ፎርማሊቲ ሁሉ ካሟላና በቤቴል ቤተክርስቲያን ከተባረከ በኋላ በAugust—September/ 2021 ላይ አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ፣ በየአገሩ የሚጠየቀውን መመዘኛ አሟልቶ ፈቃድ ለማውጣት፣ የአካባቢ መዋቅር ለማደራጀትና መነሻ ፕሮጀክቶችን ለማጥናት የመጀመሪያውን የተልዕኮ ጉዞ ወደ **ኢትዮጵያና ደቡብ አፍሪካ** ተደርጎ ሁሉም ዕቅድ እንዲከናወን እግዚአብሔር ረድቶናል።

በዚህ ጉዞ የታቀዱና የተከናወኑ ሚከተሉት ናቸው፡-

1. በመንፈሣዊ አገልግሎት ረገድ፡-

በኢትዮጵያና በደቡብ አፍሪካ በአካል በመገኘት በዚያ ለሚገኙ አብ/ክርስቲያናት መሪዎች አገልግሎቱን የማስተዋወቅ ተግባር ከመከናወኑም በላይ በሁለቱም አገራት፡-

- ◆ ከትውውቁ በኋላ ጠቅላላ ጉባኤዎች ተመሥርተዋል
- ◆ አገልግሎቱን የሚመሩ ቦርዶች ተቋቁመዋል
- ◆ የአገልግሎት ማስተባበሪያ ቢሮዎች ተከፍተዋል
- ◆ አገልግሎቱን የሚያስተባብሩ ሠራተኞች ተመድበዋል
- ◆ እንደየ አገሮቹ ሥርዓት በሕግ የማስመዝገብ ተግባር ተከናውኗል
- ◆ የባንክ ሂሣብ ተከፍቷል
- ◆ በደቡብ አፍሪካው ቦርድ ድጋፍ አንድ ሚሲዮናዊ ተሠማርቷል
- ◆ ከአንድ ቤተ ዕምነት ጋር በትብብር አራት ሚሲዮናውያንን ለመላክ ስምምነት ተደርጓል
- ◆ ከበርካታ አብያተክርስቲያናትና አጥቢያዎች ለተውጣጡ መሪ አገልጋዮችና ለሌሎችም የአገልግሎት ክፍሎች ስለ መጽሐፍ ቅዱሣዊ ደቀመዝሙርነትና ስለ አገልግሎት ሴሚናሮች ተሰጥተዋል

2. በሰብአዊ አገልግሎት ረገድ፡-

- ◊ በሰሜን ኢትዮጵያ ገጠር አካባቢ ያሉ የዛፍ ሥር ት/ት ቤቶች ግንባታን አስመልክቶ ወደ ክልሉ ድረስ በመሔድና ከኃላፊዎች ጋር በመገናኘት የዳሰሳ ጥናት ተደርጓል
- ◊ በአዲስ አበባ ከተማ ከ HIV/AIDS ጋር ለሚኖሩ 6 ቤተሰብቦች ወርሐዊና ቋሚ ዕርዳታ ተጀምሯል
- ◊ የውሀ ቁፋሮ ዋጋ ማቅረቢያ (Proforma) ተሰብስቧል
- ◊ ከጋንዲ የማዋለጃ ሆስፒታል ኃላፊዎች ጋር በመገናኘት የሆስፒታሉን አሣዛኝ ገጽታ ምልከታ ከተደረገ በኋላ ወደ አሜሪካን አገር ተመልሰን ክርስቲያን ወገኖችንና ድርጅቶችን ትብብር በመጠየቅ የማዋለጃ አልጋዎችን ጨምሮ ግምቱ $452,317.43 (አራት መቶ ሃምሣ ሁለት ሺህ ሦሥት መቶ አሥራ ሰባት የአሜሪካን ዶላር በላይ) በብር ሲታሰብ ከ23 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ የሕክምና መሣሪያዎች፣ መድኃኒቶችና ቁሣቁሶችን የያዘ ባለ 40 ጫማ ኮንቴነር ከአሜሪካን አገር አጓጉዘን ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አስረክበናል።
- ◊ ይህም መድኃኒትና የሕክምና ቁሣቁስ ከጋንዲ ሆስፒታል ሌላ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት የተጎዱ ሆስፒታሎችን መልሶ ለማቋቋም የሚደረገውን ርብርብ ለማገዝ ይውላል።
- ◊ አገልግሎቱ በአንድ ጉዞ ብቻ ይህንን ያከናወነ ሲሆን ወደ ፊት በእግዚአብሔር ኃይልና ጸጋ ይቀጥላል።
- ◊ **አገልግሎቱን ለመደገፍ በሚቀጥለው ገጽ የተመለከቱትን መንገዶች ይጠቀሙ።**

# DISCIPLESHIP NETWORKING & ADVANCEMENT OF THE KINGDOM MINISTRIES

DNA የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት

**To donate,**
**please use either of the following info.**

**Mail checks to : 8108 Montevina Drive, Sacramento, CA 95829**

*** When you write check make payable to "DNA" please**

**Call us at: Phone # (916) 224-8939**
**Go to our Website: https://www.DNAKingdomMinistries.org**

**PayPal at: DNAKingdomMinistries@gmail.com**

**"ከድሮ ዘመን የፈረሱት ሥፍራዎች ይሠራሉ፤ የብዙ ትውልድም መሠረት ይታነጻል" (ኢሣ 58፡12)**

**በባሕሪይ ግንባታ የቤ/ክንን ተሐድሶ ማፋጠን**